ኢትዮጵያችን

*ወቅታዊ አተታ*

ኢትዮጵያችን ቅጽ 6 ቁጥር 1 ጥር 21 ቀን 2015 ዓ.ም.

# <u>*ዓሣ ጎርጓሪ ...?*</u>

*የዘር ፍጅት እያካሄደ የመጣው የወያኔ/ኢሕአዴግ ቀጣይ አገዛዝ "ብልጽግና" የመጥፊያውን ክብሪት ለኩሷል። ህዝብ ከቀዬው ቢፈናቀል፣ በገጀራ ቢታረድ፣ በጦርነት ቢማገድ፣ ዘግናኝ የኑሮ ሁኔታ ውስጥ ቢዘፈቅ፣ ታሪኩ ቢንቋሸሽ፣ ጀግኖቹ ቢሰደቡ፣ አልበገር ማለቱና ሀገራዊ ፍቅርና ብሔራዊ ስሜቱ ከቶውንም ሊሸረሸር ባለመቻሉ እብደትና ንዴት ውስጥ የተዘፈቀው አገዛዝ የኢትዮጵያን ዋልታና ምሰሶ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶን ቆስቁሶ ሊወጣው የማይችለው የቁልቁለት ገደል ላይ እየተንደረደረ ይገኛል።*

*"ኢትዮጵያ ሀገራችን ዛሬ እውን ልትበታተን ወይስ ልትጠፋ ይሆን?" ብለን ስጋት ከቦናል። አዎ ከቅርብ ታሪክ አለመማር ነው እንጂ ሀገራችን ሳትሆን አንጠራጥር አሁን ያለው መንሥት ግን ሊጠፉ ወይም አወዳደቁ ሳያምር ሊወድቅ እየተንደረደረ ነው። የዋልድባ ገዳምን የሸንኮራ እርሻ ለማድረግ በመነካካታቸው በሳምንታት ውስጥ መለስ ዜናዊና አባ ጳውሎስ የተቸ፟ራቸውን ተከታታይ የአምላክ ፍርድ የዘነጋው የዶር ዐብይ አሕመድ አገዛዝ ዛሬ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሲኖዶስን ሲፈታተን ፍርዱን ለማግኘት ሲቃረብ እንደሆን ሁኔታዎች ገሀድ እየወጡ ነው።*

*ወደ ፖለቲካው እንቃኝ ካልን የቅርቡ የአንዳንድ ሚኒስትሮች ከስልጣናቸው እንዲነሱ መደረግ ደርግ መውደቂያው የመጨረሻ ሰዓታት ላይ አብረውት ያጨበጨቡትን የመግደል አቅሙ ቢሟጠጥም ከሥልጣናቸው መነሳታቸውን እንደማንኛውም ዜጋ በሬድዮ ያደመጡት ፍቅረ ስላሴ ወግደረስና ደበላ ዲንሳ ከሚጠቀሱት ውስጥ ነበሩ። መለስ ዜናዊም ከእልፈቱ መጨረሻ ሰዓት ላይ እነ ስዩም መስፍንን እና ገነት ዘውዴን መሰል አረመኔዎች ከአጠገቡ ሲያርቅ የማብቂያው ደወል ነበር። እናማ ዛሬም በዶ/ር ዐብይ አገዛዝ ውስጥ የሚታየው ከሥልጣናቸው ተነሱ፣ መልቀቂያ ጠየቁ ዜናዎች ጤናማና የተስተካከለ አገዛዝ ሳይሆን እየተፈረካከሰ መሆኑን መገንዘብ አያዳግትም። ለሀገር እና ህዝብ የተመኙት መበታተንና መፈረካከስ ወደ አገዛዙ ሲጠቁም እሰየው እንጂ ሊያስፈራ ወይም ሊያሰጋ አይገባውም።*

*ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን በአብዛኛው እንደሚስማሙበት ኢትዮጵያን ለማዳከምና ለመበታተን አንዱ መንገድ እምነቷን በተለይ ኦርቶዶክስ እምነት ላይ ያነጣጠረ ጥቃት ነው። ይህ ደግሞ ጥንት ጀምሮ በዘመነ ዮዲት ጉዲት፣ በግራኝ አሕመድ ወረራ ወቅት በዘግናኝ መልኩ ተሞክሮ ሀገር/ቤተ ክህነት ወድማ፣ ህዝብ ተጨፍጭፎ ዳግም ያንሰራራች ሀገር እንደነበረች ታሪክ መዝግቦታል። በጣሊያን ወረራም ወቅት አቡነ ጴጥሮስን ጨምሮ በርካታ ምህመናንን ሕይወት ያጣች ቤተ ክርስቲያን፣ ንብረትና ቅርሶቿን የተዘረፈች በህዝቧና በምህመናኑ ታላቅ ተጋድሎና ጸሎት እስከዛሬ አለች ወደፊትም ትኖራለች።*

*በትንሹ ከአንድ ሺህ ሰባት መቶ ዓመታት በላይ ዕድሜ ያላት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ኢትዮጵያን እንደ ሀገር ይዛ መቆየቷ የማይካድ ሀቅ ነው። ቤተክሲያኗ ዛሬ የምንጠቀምበትን የፊደል ሆዬሄት ቀርጻ ያስተማረች፣ ሀገር ብትወረር ታቦቷን ይዛ የዘመተች፣ ግብረገብን ያስተማረች፣ "ሃይማኖት የግል ሀገር የጋራ ነው" ብላ ሌሎች ሃይማኖቶችን ፈቅዳ ያከበረች፣ ምንጊዜም የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ የምታውለበልብና ስለ ሀገር ሉዓላዊነትና ስለ ህዝባችን አንድነት ስትሰብክ የኖረች ወደፊትም የምትቀጥል*

*ነች። እስከዛሬ በተፈራረቁት አገዛዞች ራሳቸው እንደፈለጋቸው ሊቃኙት የሚፈልጉት ፓትሪያርክ እና ጳጳስ ቢያሾሙም በሲኖዶስ ላይ ሌላ ሲኖዶስ ለመመስረት የተሞከረበት አሳፋሪ ድርጊት ለመጀመሪያ ጊዜ በብልጽግና አገዛዝ አስተናግዳለች። ይህም የሚያመለክተው ኢትዮጵያ እንደ ሀገር እንዳትቀጥል ፍላጎት ላላቸው ሁሉ የኦርቶዶክስን እምነት ማጥፋትና ማጥቃት አንዱ ግባቸው ነውና እምነታቸው እብደት የሆነ ትግላቸው ከፈጣሪ ነውና ለምላሹ ይዘጋጁበት።*

"ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ረዥም ዕድሜ ጋር ሲተያዩ - ከካቶሊክ በቀር - ሌሎቹ የ'ፕሮቴስታንት' ሃይማኖቶች ወደ ኢትዮጵያ ከገቡ ቢበዛ የ70 ብዙዎቹ ደግም የ50 ወይ 40 ዓመታት ዕድሜ ያላቸው ናቸው። መሠረታቸውም ወይም 'እናት' ቤተ ክርስትያናታቸው የሚገኙት በአብዛኛው በአሜሪካ ነው። በኢትዮጵያ ፀንታ ከቆመችው ኦርቶዶክስ ሃይማኖት ጋር ትከሻ ሲለካኩና ስለርሷም 'ትንቢት' ሲናገሩ ያስደንቃል" ::

*የብልጽግና ኦሮሙማ አገዛዝ ያለፈውን አምስት ዓመት ኦሮሚያ የሚለውን ህልሙን ለማሳካት መሳሪያውን ተማምኖ ግዛቱን እያሰፋ ተጉዟል። ለዚህ ደግሞ ጥርጊያው ይመቻችለት ዘንድ የአማራው ዘር ባላባራ መልኩ እየተጨፈጨፈ ነው። በሰላምና እርቅ ስም ለወያኔ/ህወሓት እውቅና ተሰጥቶ ሌላ ደባ እየተሸረበ ነው። አዲስ አበባን የኦሮሚያ ዋና ከተማነቷን ለማረጋገጥ ያልተሰራ ግፍ የለም። እጅግ በርካታ ቦታዎች ወደ ኦሮሚያ እየተካተቱና በከተማዋም የቦታ ወረራ በሰፊው ተካሂዷል። ትምህርት ቤቶች የኦሮሚያ ባንዲራ እንዲያውለበልቡና የኦሮሚያን መዝሙር እንዲዘምሩ ይደረግ የነበረው ጫና ምን ያህል የአዲስ አበባን ነዋሪና ተማሪዎችን እንዳስቆጣ የሚዘነጋ አይደለም። "የጥፋት መጨረሻው እራስን መብላት" ነውና የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ከክርስቲያን ወገኖቻቸው ጋር እንዲጋጩና ሀገር ወደ ሃይማኖት ብጥብጥ እንድትዘፈቅ የተሸረበው ሴራ አልሳካ ቢል "የመንግስት ዓይነ ደረቅ" እንዲሉ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያንን እየበጠበጡ ምንም እንዳልተፈጠረ ሀገር ሲኅበኝልን፣ ዜና ዘጋቢዎች አልሰማንም ሲሉ በታሪክ ምን ያህል ጥቁር ነጥብ ጥለው እንደሚያልፉ ሊገባቸው ይገባል።*

*ጥር* 18 *ቀን* 2015 *ዓ.ም. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሲኖዶስ ያወጣው መግለጫ የቤተ ክርስቲያኗን ጠንካራ አቋምና የምህመናኑን ጥንካሬ የሚያሳይ ብቻ ሳይሆን አሁን ያለው አገዛዝ ኢትዮጵያ አትጠፋም እያለ ሊያጠፋት፣ አትፈርስም እያለ ሊያፈርሳት የሚጓዝበትን የረቀቀ ባዶ አካሄድ ቁልጭ አድርጎ ያሳያል። የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ከመላው ዓለም ይጠፋ ዘንድ ከጥንት ጀምሮ የነበረን ሴራና ተንኮል ለተንታኞች እንተወውና ኢትዮጵያችን ላይ አጎራባች የአረብ አገራት ሳይቀሩ የማይሸርቡት ተንኮል እንዳልነበር ግልጽ ነበር። ባዕዳን ኃይሎች ሀገር በቀል የፖለቲካ ድርጅቶችን በመርዳት የተቻላቸውን ጥረው አልተሳካላቸውም። አሁን ላለው አገዛዝ ደግሞ የተቻላቸውን ያህል በቢልዮን ዶላር እያፈሰሱ የመንግሥት አቅጣጫ ወደ ልማት እያስመሰሉ በጦርነት ሲያምሱን፣ በዘረኝነት አንድ ዘር ሲጨፈጭፉ፣ ታሪካችንን ሲያንቋሽሹ፣ መለያ ሰንደቅ ዓላማችንን ሲረግጡ አልበቃ ቢላቸው ያደፈጡ ተኩላዎችን ሰግስገው በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ላይ ዘምተዋል።*

*ኢትዮጵያ በዘር ሕገ መንግሥት የምትተዳደርበት ዘመን እያበቃ ነው። አሁን የዶር ዐቢይ አገዛዝ መወገድ ብቻ ሳይሆን ዘረኝነት ወድሞ ዘርንና ቋንቋን ተገን ያደረገ አገዛዝ አብቅቶ፣ ህዝባችን ላይ የተጫነው የኑሮ ውድነት ጋብ ብሎ በየወቅቱ ህዝብን ያለአግባብ ማፈናቀል አብቅቶ ኢትዮጵያዊ ብሔራዊ ስሜት ያለው መንግሥታዊ ሥርዓት ይመሰረት ዘንድ መታሰብ ያለበት ወቅት ላይ ተደርሷል። እስከዛሬ እንዳየነው የዛሬው መንግሥት ከነገ ይሻላል እንዳያስብለን በጥንቃቄ መጓዝና ማገናዘብ እሚገባን ወቅት ላይ ተደርሷል። የሀገራችን እጣ ፈንታ ያለው በህዝባችን ትከሻ ላይ ነውና በተደጋጋሚ ያየናቸውን ከሃዲ የውጭ ኃይሎች በተለይ ምዕራብያውያንን ለመማጠን የምናባክነውን ጊዜና ገንዘብ የሀገሪቷንና የዓለም ፖለቲካን ከማዛባት የሚፈጠር ስህተትን አንዳንድ ምሁራን አካሄዳቸውን መርምረው ከህዝብና ሀገር ጎን ተሰልፈው  አቅጣጫ ለመስጠት ቢተጉ መልክም ይመስለናል።*

ይህ ዘረኛ አገዛዝ ቡድን አካበትኩ በአለው መሣሪያውና የጦር ኃይሉ ታውሯል፣ አለማሁ በአለው ስንዴ በጥጋብ ተወጥሯል፣ በለጸግሁ/ሠራሁ ባላቸው ፕሮጀክቶች አቅሉን አጥቷል። አሁን በሀገራችን የተከሰተው ሁኔታ ከአንድ ተቃዋሚ/ተፎካካሪ የፖለቲካ ድርጅት ጋር ሳይሆን ከእምነት ጋር ነው። እምነት ደግሞ ያውም የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ሠራዊቱ ውስጥ አለ፣ ምክር ቤቱ ውስጥ አለ፣ ሚኒስትሮች ምክር ቤት አለ፣ ኦሮሞዎች፣ ትግሬዎች፣ አማራው፣ ጉራጌው፣ ደቡቡ፣ ምሥራቁ፣ ምዕራቡ ህዝብ ጋ ብቻ ሳይሆን ለዘመናት አብሮ የኖረው ሙስሊሙ ህብረተሰብ ዘንድ መኖሩን እንዳንጠራጠር። በመሆኑም በእምነት የመጣ ትንኮሳ <u>“ዓሣ ጎርጓሪ. . .?”</u> እንዲሉ መንግሥት አወዳደቁን ያሳምርልኝ ቢል እንኳ አምልጦታልና ሀገራችንስ ተገላገለች ወዬው ለናንተ!

የዶር ዐብይ አገዛዝ ከወያኔ/ህወሓት ውስጥ ብቅ ብሎ እንዴት ለዛሬ ሥልጣን እንደበቃ ቢመረምር በቂው ነበር። ወያኔ/ህወሓት ከመሳሪያው እና ሙሉ በሙሉ በአንድ ዘር ከመታጠሩ በላይ አንድ ለአምስት በሚል የስለላ ወጥመዱን ህዝቡን ጠንፍሮ ከውጭ የሚመጣ ተፋላሚ ሲጠባበቅ ነው ከወያኔ ቀንድ አውጣ ዶር ዐቢይ መዘዝ ያለውና መሸወድ ካልነው “ኢትዮጵያ! ኢትዮጵያ! ኢትዮጵያ!” ብሎ ህዝብ ያስጨፈረውና ዛሬ በተገላቢጦሽ “ኦሮሚያ ኦሮሚያ ኦሮሚያ” የሚዘመርብን። ከራሱ የቅርብ አመጣጥ ያልተማረ አገዛዝ እምነት ያህልን ከባድ መንፈስ ተንኩሶ በረከቱ መርገም፣ አወዳደቁ መፈጥፈጥ እንደሚሆን መናገር ትንቢተኝነት አይደለም።

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኖራለች!

ፈጣሪ ኢትዮጵያንና ህዝቧን ይባርክ!

**ጥር 21 ቀን 2015 ዓ.ም.** (January 29, 2023)

ኢሜል ፡ ethiopiachen2009@gmail.com
ድረ ገጽ ፡ www.ethiopiachen.org , www.ethiopiachen.com
ምሥለ ገጽ ፡ ıHıH Ethiopiachin